**በአዲስ አበባ ከተማ  አስተዳደር የኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ**

**ትምህርት ጽ/ቤት**

የ6ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና

ግብረ ገብ ፡- 2016 ዓ.ም (2024 እ.ኤ.አ)

የጥያቄ ብዛት፡- 40          የተፈቀደው ሰዓት፡- 1፡00 ሰዓት

**አጠቃላይ ትዕዛዝ**

ይህ የግብረ ገብ ምህርት ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል ፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤ በመልስ መስጫ ላይ ትክክለኛው መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው ፤ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መፅዳት አለበት፡፡

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ፡00ሰዓት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመሰሪያነት የምንጠቀምበትን የመፃፊያ እርሳስ ማስቀመጥና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን ፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችሁ ተቀምጣችሁ መጠበቅ አለባችሁ፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናውን ሕግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም ፤ ፈተናውን እንዳይፈተኑም ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት መልስ መስጫው ላይ መሙላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት ፡፡

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር  ክልክለክ ነው !**

**በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ተማ የ6ኛ ክፍል የክፍለ ከተማው የመጀመርያ ሴሚስተር የሞዴል ፈተና ።**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፍደል በመምረጥ የመልስ መስጫው ላይ መልሱን አስቀምጡ ።

1. የመልካም ጠባይ ( ባሕርይ ) ምንነትን የያዘው ፊደል የትኛው ነው?
   ሀ. የሰዎች እምነትና አስተሳሰብ ውጤት ነው ።
   ለ. መልካም ና ጥሩ ሥነ ምግባር መያዝ ነው ።
   ሐ. በአርያነትና ብምሳሌነት በመልካም የሚነሳ ጠባይ መያዝ ነው ።
   መ. ሁሉም መልስ ነው ።
2. ሰዎችን ማክበር የሚያስገኘው ጥቅም ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛው የትኛው ነው?

   ሀ. ለስኬታማና ውጤታማነት ያበቃል ለ. እኛንም ሌሎች ሰዎች እንዲያከብሩን ያደርጋል

   ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው መ. መልስ አልተሰጠም

3. የመልካም ባሕርይ ( ጠባይ) ምሳሌ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. በራስ መተማመን ለ. ፈቃድን መጠየቅ
   ሐ. ትኑት መሆን መ. ሁሉም መልስ ናቸው
4. መልካመረ ባሕርይ የብዙ ምክንያቶች ድምር ውጤት እንደሆነ ይነገራል ። ከሚከተሉት መካከል የትኛው ትክክለኛ ምክኒያ ነው ?
   ሀ. ቤትሰብ ለ. ጊዜ ሐ. ምርጫ መ. ሁሉም መልስ ናቸው
5. መልካም ባሕርይ ( ጠባይ ) ያለው ሰው መገለጫው የሆነውን ምረጡ?

   ሀ. ምልዑት ለ. ታማኝነት ሐ. ምርጫ መ.ሀ እና ለ መልስ ናቸው

6. ራስን መቆጣጠር ማለት …………….. ማለት ነው?

   ሀ. ስሜትን ና ምኞትን መግታት ለ. የሌሎችን ንብረት መቆጣጠር

   ሐ. በራስ መተማመን መ. ሁሉም መልስ ናቸው

7. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሀቀኛ ሰዎች መለያ ባሕርያት ( ጠባያት ) የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. እውነትን መናገር ለ. ማጭበርበርን ማበረታታት
   ሐ. ስህተትን መቀበል መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው
8. ከሚከተሉት ምርጫዎች ውስጥ የአክብሮት ፅንሰ ሃሳብ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ወላጆችን ና ታላላቆችን ማክበር ለ. ሽማግሌዎችን ማክበር
   ሐ. ሰውን ሁሉ በእኩልነት ማክበር መ. ሁሉም መልስ ናቸው
9. የመልካም ባሕርይ ( ጠባይ ) የመላበስ ጠቀሜታ ምንድን ነው?
   ሀ. ግብረ ገባዊነትን ያዳብራል ለ. ለሰላምና ፀጥታ ትልቅ አቅም ይፈጥራል
   ሐ. ስምምነትን ያመጣል መ. ሁሉም መልስ ናቸው
10. የሀቀኛ ሰዎች መለያ ጠባያት ( ባሕርያት ) ከምንላአቸው መካከል ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
    ሀ. አለማጭበርበር ለ. ሙስናን መውደድ ሐ. እውነትን አለመናገር መ. መልሱየለም
11. አክብሮት ማለት …………… ማለት ነው ?
    ሀ. ትኑት መሆን ለ. መታዘዝ ሐ. ግጭትን ማስወገድ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

12. እራስን ማክበር በተመለከተ የሚገልጸው የትኛው አማራጭ ትክክል ነው?
   ሀ. በራስ መተማመንና መኩራት ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው
   ለ. እራስን መንከባከብ መ. መልስ የለም
13. ወላጆችን ማክበር መገለጫው ምንድን ነው?
   ሀ. በመታዘዝ ለ. እግር በማጠብ ሐ. በመቆጠት መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው
14. መልካም ጠባይ ( ባሕርይ ) ማሳደጊያ ዘዴዎች ከሚከተሉት ትክክለኛውን ምረጡ?
   ሀ. ራስን መቆጣጠር ለ. ለሕግ ተገዥ መሆን ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው መ. መልሱ አልሰጠም
15. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛ የግብረ ገባዊ መዝገበ ቃል ፍች የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. መቻቻል ለ. ምግባረ ቀና ሐ. ግልፀኝነት መ. መልስ አልተሰጠም
16. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ምልዑነት ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ከሌሎች ምክር መጠየቅ ለ. ለሌሎች ክብር መስጠት
   ሐ. ኢ - ተለዋዋጭ መ. ሁሉም መልስ ናቸው
17. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሕይወታችንን በምልዑነት ለመምራት ይጠቅማል ።
   ሀ. በገንዘብ ሀብታም ሆኖ መገኘት ለ. የቤተሰቦችን እርካታ መጠበቅ
   ሐ. ስኬታማ መሆን መ. ሀቀኛ መሆንና በራስ መተማመን
18. ............ አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር እንዲተገበር የሚያደርግ ውስጣዊ ችሎታ ነው ።
   ሀ. በራስ መተማመን ለ. ድፍረት ሐ. ሀቀኛነት መ. ተጠያቂነት
19. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረ ገብ ምልዑነት ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው ?
   ሀ. የሀገር እድገት ያፋጥናል ለ. ሙስኝነትን ይቀንሳል ሐ. የት/ት ጥራትን ይጨምራል መ. መልሱ የለም
20. ከሚከተሉት ምርጫ መካከል የግብረ ገብ ምልዑነት አለመኖር የሚያስከትለው ችግር ምንድ ነው?
   ሀ. ግብር ለ. ሰብአዊ መብት ሐ. ግብር ሥወራ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው
21. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የግብረ ገብ ምልዑነት የተላበሰ ሰው መገለጫ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. በራስ መተማመን ለ. ሀቀኛነት ሐ. ርኅራኄ መ. ሁሉም መልስ ናቸው
22. ........... ማለት ነገሮችን በራሳችን የነከወን ዓላማችንን የማሳካት ብቃት እንዳለን መቀበል ነው ።
   ሀ. ኃላፊነትን መቀበል ለ. በራስ መተማመን ሐ. ከጥገኝነት መላቀቅ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

23. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ሕግ ጠቃሚ የሆነው የትኛው አማራጭ ነው?
   ሀ. የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ያስጠብቃል ለ. የባለሥልጣናትን ሥልጣንና ኃላፊነት ይገድባል
   ሐ. የዜጎችን ነፃነት ያስከብራል መ. ሁሉም መልስ ናቸው
24. ከሚከተሉት ምርጫዎች መካከል ለሕግ ተገዥነት አስፈላጊነት ወስጥ የሚካተተው የቱ ነው?
   ሀ. ፍትሐዊ የሀብት ክክፍፍል እንዲኖር ለ. ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ
   ሐ. የዜጎችን ፍላጎት ለማሟላት መ. ሁሉም መልስ ነው
25. ........... ማለት ዜጎች ሰው በመሆናቸው ብቻ በተፈጥሮ የሚያገኙት የመብት ዓይነት ነው?
   ሀ. የማኅበረሰሰብ መብት ለ. ሰብአዊ መብት ሐ. ዴሞክራሲያዊ መብት መ. መልሱ አልተሰጠም
26. ......... ማለት አንድ ሀገር በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የምትመራ ከሆነ ለዜጎቿ የምትሰጠው የመብት ዓይነት ነው።
   ሀ ሰብአዊ መብት ለ. ዴሞክራሲያዊ መብት ሐ. ፖለቲካዊ መብት መ. ሁሉም

27. _………. ማለት ሥልጣን ባላቸው ግለሰቦች የሚፈፀም ሕገ ወጥ ተጋባር ነው?
   ሀ. ግብር ሥወራ ለ. ሙስና ሐ. ሕገወጥ የሕፃናት ዝውውር መ. ሁሉም
28. _ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የሙስና ዓይነት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የዝምድና ወገንተኝነት ለ. ጉቦ መስጠት ሐ. ማጭበርበር መ. ሁሉም
29. ራስን መቆጣጠር ( መግዛት ) ሲባል ………… ማለት ነው ?
   ሀ. ስሜትንና ምኞትን መግታት ለ. በራስ ላይ ማዕቀብ መጣል
   ሐ. ራስን መጣል መ. መልሱ አልተሰጠም
30. የሕብረተሰቡ <u>እሴት</u> መጠበቅ ሲባል <u>………..</u> ማለት ነው የተሰመረበት ቃል ትርጉም ምን ማለት ነው ?
   ሀ.ዝርዝር ለ. ከፍታ ሐ. ጥምን ( ዋጋን) መ. ሁሉም
31. በኢትዮጵያውያን መካከል የሚገኙ የግብረ ገብ እሴቶች ውስጥ ምሳሌ የሆነው የሆነው የቱ ነው ?
   ሀ. እንግዳ ተቀባይነት ለ. ሥርዓት አልበኝነት ሐ. ስጦታን በሁለት እጅ አለመቀበል መ. ሁሉም
32. መልካም ጠባይ ( ባሕርይ ) አለመላበስ የሚያስከትላቸው ውጤቶች መካከል የሆነው የቱ ነው ?
   ሀ. ታማኝ አለመሆን ለ. የእርስ በእርስ ግጭት ሐ. የፈተና ኩረጃ(ስርቆት ) መ. ሁሉም
33. ጠባይ ( ባሕርይ ) በ………. የሚመጣ ውጤት ነው ፡፡ ከሚከተሉት ውስጥ ባዶ ቦታውን የሚያሟላ ትክክለኛው ቃል የቱ ነው
   ሀ. ምርጫ ለ. በጦርነት ሐ. ባለመስማማት መ. በግጭት
34. ጊዜ የጠባይ ( የባሕርይ ) መለወጥ ምክንያት እንዴት እነደሆነ የሚገልጸው አማራጭ የትኛው ነው
   ሀ. ልጆች የባሕርይ ለውጥ የሚመጡት በሂደት ነው ለ. ጊዜ ለሥራ አመች በመሆኑ
   ሐ. ጊዜን በማባከን መ. ሁሉም
35. ራስን በሌሎች ቦታ አድርጎ ማየት ማለት ……… ማለት ነው
   ሀ.የሌሎችን ሰዎች ስሜት መረዳት ለ. እሌላ ሰው ላይ የሆነው እኔላይ ቢሆንስ ብሎ ማሰብ
   ሐ. ችግርንና ጉዳትን መጋራት መቻል መ. ሁሉም
36. የሕግ ተገዥነት አስፈላጊ እና ጠቃሚ የሆነው የቱ ነው
   ሀ. ሙሉ ነፃነት ለ. ሰላምን መጠበቅ ሐ. ፍትሐዊነትን ማምጣት መ. ሁሉም
37. ከሚከተሉት አማራጮች የሰላም ዓነቶች ከሚባሉት መካከል የትኞች ናቸው
   ሀ. አሉታዊና አውንታዊ ለ. ይሁንታዊና እምቢታ ሐ. የሰላም እጦት መ. ሁሉም
38. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የሙስና ትርጉም የያዘው የትኛው ነው ?
   ሀ. ሥልጣን ባላቸው ግለሰቦች የሚፈፀም ያለመታመን የወንጀል ባሕርይ ነው
   ለ.ሙሰኞች ጎቦን የሚቀበሉት ሕዝብን ለማገልገል ነው
   ሐ. የሙስና መገለጫ ባሕርይ የለውም
   መ. ሁሉም
39. ሕገ ወጥ የሕፃናት ዝውውር የሚካሄደው ከሚከተሉት ለየትኛው ጉዳይ ( ሥራ) ነው ፡፡
   ሀ. ለጉልበት ብዝበዛ ለ. ለአስገዳጅ ሥራ ሐ. ለወሲባዊ ጉዳይ መ. ሁሉም

40. የፍትሕ እጦት ስንል ምን ማለታችን ነው ?
   ሀ. ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ ቅጣት አለመጣል ለ.በተለያዩ ምክንያቶች ና መደለል ተበዳይን አለማርካት
   ሐ. ወንጀለኛውን ለመጥቀም መወሰን መ. ሁሉም መልስ ናቸው